## •••• (CAOMI) ውስጥ ላሉ · · · · · · · · · · · · · · · · · ·

ለጥቂት ወራት (እንደ ፈረንሳይ ባለስልጣናት መረጃ ከሆነ ከሶስት ወራት ላልበለጠ) መቆየት ወደምትችሉበት ካኦሚ(CAOMI) ወደተባለ መጠለያ ማዕከል ተልካችⅡል፡፡

ለመልቀቅ ነፃ ናችሁ፣ ነገር ግን በዚህ ማዕከል ለመቆየት አሳማኝ ምክንያት አላችሁ፤ ምክንያቶችም ለማረፍና ወደ ዩናይትድ ኪንግደም(ዩኬ) ለመሄድ ወይም በፈረንሳይ ውስጥ ለመቆየት የሚያስችሉ አስፈላጊ ማመልከቻዎችን መጀመር ናቸው፡፡

ፈረንሳይ ማንኛውም ወደ ዩኬ ለመሄድ ፍላጎት ያለውን ሰው ጥያቄ ተቀብላ ትመረምራለች፡፡ የብሪቲሽ ባለስልጣናት ደግሞ የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ የእናንተ ሁኔታ በሚቆዩበት ማዕከል ውስጥ ይጠናል፡፡ ነገር ግን ወደ ዩኬ የመሄድ ፍላጎት ጥያቄ አቅራቢዎች ማለትም የተወሰኑት እንጂ የጠየቁት በሙሉ አይፈቀድላቸውም፡፡

በፈረንሳይ ለመኖር የሚፈልጉ (ወይም ወደ ዩኬ ለመሄድ ጠይቀው ፈቃድ ያላገኙ) በአደጋ ጊዜ ከአስራ ስምንት አመት በታች የሆኑ ወጣቶች (በተለይም በወላጆች ጥበቃ ስር ያልሆኑ) በፈረንሳይ ባለስልጣናት የሚሰጠውን ጥበቃ ወይም ከለላ ያገኛሉ፡፡ ይህም «የህጻናት ጥበቃ » ተብሎ ይጠራል፡፡

ከ 18 አመት በታች የሆኑት ከዚህ ከለላ ወይም ጥበቃ ተጠቃሚ ለማድረግ ከህጻናት ጥበቃ አገልግሎት የሚነሱ ጥያቄዎችን መመለስ ይገባል(« Aide sociale à l'enfance »፣ ኤኤስኢ ) ወይም ለኤኤስኢ የሚሰሩ ማህበራት፡፡

ኤኤስኢ የፈረንሳይ ግዛት ክፍል አይደለም፣ ነገር ግን ከክፍሉ (ፈረንሳይን ከመሰረቷት 100 አነስተኛ ግዛቶች ውስጥ አንዱ ነው)፡፡ ኤኤስኢው እድሜያችሁ ከአስራ ስምንት አመት በታችና በፈረንሳይ ውስጥ ብቸኛ መሆናችሁን ያረጋግጣል፡፡ እድሜያችሁን የሚያሳይ መታወቂያ ወይም የልደት ምስክር ወረቀት ካላችሁ ለኤኤስኤው አሳዩ፡፡ መግንዘብ የሚገባችሁ ነገር ቢኖር ኤኤስኢው እነዚህ የምታቀርቡዋቸው ወረቀቶች ወይም ማስረጃዎች ከአገራችሁ ለመሆናቸውና እውነተኛ ለመሆናቸው ያረጋግጣል!

ወረቀት ከሌላችሁ (ወይም ከጠፋባችሁ)፣ ችግር የለውም፡፡ ኤኤስኢው እድሜያችሁን፣ ስለቤተሰባችሁ ሁኔታ (ቤተሰባችሁ በህይወት ካሉ፣ የት እንደሚኖሩ፣ ወንድምና እህቶች ያላችሁ መሆኑንና አለመሆኑን፣ ካላችሁ የነርሱን እድሜ)፣ በሀገራችሁ ውስጥ ስነበረው ህይወታችሁ ማለትም (በስራ፣ በትምህርት) እንደነበራችሁ በምን ምክንያት ከሀገራችሁ እንደለቀቃችሁ (በአደጋ፣ በቤተሰብ ችግር፣ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ) ይጠይቁዋችⅡል፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች በቻላችሁት መጠንና ባላችሁ መረጃ በመመስረት መመለስ ይገባል፡፡

ኤኤስኢው ለአካለ መጠን አለመድረሳችሁን ካወቀ ጉዳያችሁ ወደ ህጻናት ዳኛ (« juge des enfants ») ይላካል፡፡ ይህም እድሜያችሁ አስራ ስምንት እስከሚሞላ ማን እንደሚንከባከባችሁና የት እንደምትኖሩ ይወስናል፡፡ በካኦሚው (CAOMI) ውስጥ አይቆዩም፡፡ አሁን ካላችሁበት በተለየ ክፍል ወደሚገኘው የኤኤስኢ መጠለያ ይላካሉ፡፡ ይህ በርካታ ወራት ይወስዳል፡፡

ኤኤስኢው ከአስራ ስምንት አመት በታች መሆናችሁን ካላመነ ወይም ካልተቀበለ፤ ኤኤስኢው እድሜያችሁን ሊጠራጠርና ከአስራ ስምንት አመት በላይ ነው ብሎ ሊያስብ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ወደጎልማሶች ማረፊያ ወይም ማዕከል እንድትሄዱ ሀሳብ ሊያቀርቡ ይችል ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ፣ በኤኤስኢ ሰራተኛ የተፈረመ የውሳኔ ደብዳቤ ወረቀት እንዲሰጧችሁ ጠይቁዋቸው፡፡ ምክንያቱም እድሜያችሁን በተመለከተ ኤኤስኢ ስህተት ሰርቷል ብላችሁ ካሰባችሁ ወደ ልዩ ዳኛ ማለትም የህፃናት ዳኛ ማመልከት ትችላላችሁ፡፡ እኒህ ዳኛ የሚሰሩት የህፃናት ጥበቃ ብቻ ነው፡፡ ይህ/ቸ ዳኛ እዚህ የተቀመጡት እናተን ለመርዳት እንጂ ለመግረፍ አይደለም፡፡ በመሆኑም ያለ ምንም ማመንታት ኤኤስኢ ስህተት ስለሰራባችሁ እንጂ እድሜያችሁ ከ18 አመት በታች እንደሆነ በጹሁፍ ማቅረብ፡፡
ወደ ዳኛው ደብዳቤ/ማመልከቻ ለመፃፍ እርዳታ እንዲያደርግላችሁ ለትምህርት ባለሙያው መጠየቅ

ትችላላችሁ፡፡ *éducateur ወይም éducatrice* ሊረዱዋችሁ ካልፈለጉ፣ ወደ እኛ በ **07.62.48.22.07** ደውሉ፡፡ ደብዳቤውን ለመፃፍ የሚያግዛችሁ ሰው ለመፈለግ እንሞክራለን፡፡ ቀጥሎም « juge des enfants » መጣችሁ እንድታዩት ይጋብዛችⅡል፡፡የናንተን ሁኔታ በተመለከተ ለርሱ መግለጽ ትችላላችሁ፡፡ ወደ ዳኛ በምትቀርቡበት ጊዜ የህግ ባለሙያ ድጋፍ በነጻ የማግኘት መብት አላችሁ፡፡

ሀገራችሁን የለቀቃችሁት በአደጋ ከሆነ (ማለትም የማሳደድ፣ ጦርነት፣ ማስፈራራት ወይም በሌላ ምክንያት) ከሆነ በፈረንሳይ ውስጥ የጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ ትችላላችሁ፡፡ የጥገኝነት ጥያቄ ከህፃናት ጥበቃ የተለየ ነው፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ከህጻናት ጥበቃውና ከጥገኝነት ጥያቄው ተጠቃሚ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ የጥገኝነት ጥያቄ ለማቀረብ፣ ለጥገኝነት ጠያቂዎች ወደተዘጋጀው የመቀበያ መድረክ መሄድ ይገባል (« plateforme d'accueil pour demandeurs d'asile »)፡፡ በማንኛውም ክፍል የመቀበያ መድረክ አለ፡፡ ጥገኝነት ለመጠየቅ እንደምትፈልጉ ለ *éducateurs* ወይም *éducatrices* መንገር ያስፈልጋል፡፡ በማዕከላችሁ ውስጥ ሊረዳችሁ የሚፈልግ ከሌለ፣ በ **07.62.48.22.07** ወደ እኛ መደወል ትችላላችሁ፡፡

የጥገኝነት ጥያቄያችሁ በፈረንሳይ ባለስልጣናት ይመረመራል፣ ነገር ግን ዩኬ ቤተሰብካላችሁ መናገር አለባችሁ፡፡ ቤተሰብ ዩኬ ካላችሁ ፈረንሳይ ዩኬን እናንተን ወደ ግዛቷ እንድትገቡ በመፍቀድ የጥገኝነት ጥያቄያችሁን እንድትመረምር ትጠይቃለች፡፡

ለበለጠ መረጃ፣ የጥገኝነት ጥያቄ ሂደትን በተመለከተ በስድስት ቋንቋ የተተረጎመውን መረጃ በቀጥታ በድረገጽ www.gisti.org/asile-en-france ማንበብ ትችላላችሁ፡፡

አውቶብሶች ከካላይስ ሲለቁ፣ በካምፑ ወይም መጠለያው ውስጥ እርዳታ ያደረገላችሁ ማህበር ይህ **07.62.48.22.07** ስልክ ቁጥር ያለበት ወረቀት ይሰጣችⅡል፡፡ ይህ ስልክ ቁጥር የተያዘው ካሊያስ ውስጥ ድጋፍ ካደረገላችሁ ማህበር ጋርና በፈረንሳይ ውስጥ ከሚገኙ ከሌሎች ማህበራትም ማለትም የህግ ባለሙያዎች/አዋቂዎች ግንኙነት ካለው በ InfoMIE ማህበር ነው፡፡ በዚህ ስልክ ቁጥር ያላችሁበትን ቦታ ለመንገር፣ ጥያቄ ለመጠየቅ ወይም ስለ ማንኛውም ችግሮቻችሁ ለማውራት ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡ ይህን ለማድረግ፣ እባክዎን በአጭር የጹሁፍ መልዕክት (SMS) የራሳችሁን ስም፣ የአባታችሁን ስም፣ ዜግነት፣ የምትገኙበትን ከተማ፣ እድሜና የመግባቢያ ቋንቋ ላኩልን፡፡

መረጃው የተገናዘበው በ GISTI (www.gisti.org) et Infomie (www.infomie.net)፣ ኖቨምበር 2016